**አዋጅ ቁጥር ......../2011**

**የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን መብቶች በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡ ሌሎች ሰብዓዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ለማረጋገጥ ያላቸውን ፋይዳ በመገንዘብ እና በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆን መገናኛ ብዙሃን የሚጫወቱትን የማይተካ ሚና በመረዳት፤

በተለይም የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 29 (6) ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ለመገደብ የሚወጡ ሕጎች በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው መሆን እንዳለባቸው በመረዳት፤

ጥራቱን የጠበቀና ተደራሽ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን አሠራር እንዲስፋፋ ማድረግ ለፈጣንና ቀጣይነት ላለው ሁለንተናዊ ዕድገት ቁልፍ የሆነውን በመረጃ የበለፀገ ሕብረተሰብ ለመፍጠር የሚያስችልና ለሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በማመን፤

መገናኛ ብዙሃን የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ፣ እንዲሁም ተነፃፃሪ መብቶችና ጥቅሞችን ባከበረ መልኩ በኃላፊነት መንቀሳቀሳቸውን ማረጋገጥና በሕግ መሰረት እንዲሠሩ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍና ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

Preliminary Draft

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩት የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 እና የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999 የነበረባቸውን ክፍተቶች በማስተካከል ከኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የዴሞክራሲ እና የቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚጣጣም ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር ....../2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) "የመገናኛ ብዙሃን" ማለት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት፣ የብሮድካስት አገልግሎትን እና ዲጂታል የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የዜናና የፕሮግራም አገልግሎት ለብዙሃኑ ለመስጠት የተቋቋሙ አካላትን እንዲሁም የዜና አገልግሎት ድርጅቶችን ያጠቃልላል፤

2) "በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት" ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም፤ በጠቅላላው ኅብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የሕዝብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጦችንና መፅሄቶችን የሚያካት የኅትመት ስራ ነው፤

Preliminary Draft

3) “የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ሕዝብን ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት የሚተላለፍ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

4) "ዲጂታል የመገናኛ ብዙሃን" ማለት ዋነኛ ሥራው ዜናና ፕሮግራምን መሰብሰብ፣ ማጠናቀርና ማሰራጨት በሆነ ድርጅት በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ምስል፣ ድምፅ፣ ቪድዮ እና የድረ-ገፅ ፅሁፍ በመጠቀም ወይም እነዚህን በማቀናጀት መረጃ የማስተላለፍ አገልግሎት ነው፤

5) “ዜና” ማለት አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና ወቅታዊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት በብሮድካስት አገልግሎት፣ በኢንተርኔት እና በመሰል የመረጃ መረብ አማካኝነት የሚቀርብ የዘገባ ሥርጭት ነው፤

6) “ፕሮግራም” ማለት በድምፅ፣ በምስል ወይም በድምፅና በምስል ተቀነባብሮ ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅ ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት፣ በኢንተርኔት እና በመሰል የመረጃ መረብ አማካኝነት የሚቀርብ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራምና የዜና ሥርጭት ሲሆን በአገር ውስጥ ተዘጋጅቶ በማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ወደ አገር ውስጥ የተሠራጨ ፕሮግራምን ይጨምራል፤

7) “አገራዊ ፕሮግራም” ማለት በአገር ውስጥ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ፕሮግራም ሲሆን ማስታወቂያን አያካትትም፤

8) "ብሮድካስቲንግ" ማለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ለሕዝብ በድምጽ ወይም በድምጽና በምስል ማስተላለፍ እና ማሰራጨት ነው፤

9) "ብሮድካስተር" ማለት የግል ወይም የመንግሥት ድርጅትን ውስጣዊ ግንኙነቶች የማያካትትና ምድር ለምድር አስተላላፊ ትራንስሚተሮችን፣ ኬብሎችንና ሳተላይትን በመሰሉ ማሰራጫዎች አማካይነት በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን የብሮድካስት መልእክት መቀበያዎች

Preliminary Draft

ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክስ መቀበያዎች አማካይነት በክፍያ ወይም ያለክፍያ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን በአንድ ጊዜ ሕዝብ እንዲያዳምጣቸው እና እንዲመለከታቸው ወይም እንዲሰማቸው የሚያሰራጭ ሰው ነው፤

10) “የብሮድካስት ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 28 እና 29 መሰረት ወይም ወደፊት በሚለዩ የብሮድካስት ፈቃድ አይነቶች ላይ በመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ለብሮድካስት ፈቃድ አመልካቾች የሚሰጥ ፈቃድ ማለት ነው፤

11) “የብሮድካስት ባለፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሆን ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ተሰጥቶት የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ሰውንም ይጨምራል፤

12) “የፈቃድ አካባቢ” ማለት በብሮድካስት ፈቃድ ላይ የብሮድካስት አገልግሎቱን ለመስጠት ተለይቶ የተቀመጠ አካባቢ ማለት ነው፤

13) “የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በአገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ የተቋቋመ ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለክልል ምክር ቤት የሆነ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

14) “የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ትርፍ ለማግኘት በንግድ ድርጅትነት የሕግ ሰውነት ተሰጥቶት የተቋቋመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

15) “የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በማኅበረሰቡ ፍላጐት የተቋቋመ፣ በማኅበረሰቡ የሚመራ እና የሚተዳደር ለትርፍ ያልተቋቋመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

16) “ማኅበረሰብ” ማለት በአንድ አካባቢ በመኖራቸው ወይም የተለየ ማንነት በመጋራታቸው የተነሳ፣ የተለየ የጋራ ፍላጎትና ዓላማ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው፤

Preliminary Draft

17) “የአየር ሞገድን በመጠቀም የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በአለም ዓቀፍ ሥምምነት መሠረት በአለም አቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኅብረት ለኢትዮጵያ የተመደበውንና ውስን የሃገር ሐብት የሆነውን ፍሪኩዌንሲ በመጠቀም የሚሰጥ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

18) “ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት የመሬት ገፅ ላይ መሠረቱን ካደረገ ማሰራጫ በአንቴና አማካይነት ለተጠቃሚው የሚደርስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

19) “ነፃ የአየር የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ለቴሌቪዥን እቃው ከሚከፈለው የፈቃድ ክፍያ ውጭ ለብሮድካስት ባለፈቃዱ ምንም ክፍያ ሳያስፈልግ ለተጠቃሚው የሚደርስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

20) “የሳተላይት የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት የሳተላይት ኔትወርክ በማቋቋም ወይም ማንኛውንም የሳተላይት ቻናል በመከራየት የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

21) “የኬብል የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በኬብል አማካይነት የቴሌቪዥን ኘሮግራም በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

22) “የክፍያ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት የውጪ ኘሮግራሞችን በመቀበል ለደንበኞች በክፍያ የማድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

23) “አለም አቀፍ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ አድማጭና ተመልካቾች ዜናና ፕሮግራም የሚያቀርብ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

24) “አገር አቀፍ ስርጭት” ማለት ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍን የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ነው፤

Preliminary Draft

25) “ክልላዊ ስርጭት” ማለት በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ነው፤

26) “አካባቢያዊ ስርጭት” ማለት ከክልል በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ብቻ የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ነው፤

27) “ሃገራዊ ይዘት” ማለት በሃገር ውስጥ በሚገኝ የብሮድካስት አገልግሎት ወይም ነዋሪነቱ በሃገሪቱ የሆነም ሆነ ያልሆነ ዜጋ ወይም ነዋሪነቱ በሃገሪቱ የሆነ የውጭ ዜጋ ያዘጋጀው ፕሮግራም ነው፤

28) “የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ” ማለት አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት እራሱንና ዓላማውን ለማስተዋወቅ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በጋዜጣ የሚያስነግረው ማስታወቂያ ነው፤

29) "ዋና አዘጋጅ" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 47 በተደነገገው መሰረት ሙሉ የኤዲቶሪያል ሥልጣን ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

30) "አሳታሚ" ማለት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመትን የሚያሳትምና ለሥርጭት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

31) "አታሚ" ማለት የኅትመት ስራዎችን ለማተም በአሳታሚው የተመረጠ ወይም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ማንኛውም ሰው ነው፤

32) “አመልካች” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21(3) የተጠቀሰውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ ሰው ነው፤

33) “ቁጥጥር” ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን መገናኛ ብዙሃን በሕግ መሠረት መሥራታቸውንና ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን የመከታተል፣ የማረጋገጥና የማገዝ ሥራ ነው፤

Preliminary Draft

34) "የመገናኛ ብዙሃን የርስ በርስ ቁጥጥር" ማለት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው የሚገዙበትን፣ የሙያ ሥነ ምግባርና የመልካም አሰራር ደንብ የሚያወጡበትና የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ቅሬታዎች የሚያስተናግዱበትን አሠራር በመዘርጋት ራሳቸውን ለሕዝቡ ተጠያቂ አድርገው ርስ በርስ የሚግሩበት ሒደት ነው፤

35) "የመንግሥት አካል" ማለት በፌደራል ወይም በክልል ሕገ መንግሥት ወይም በሌላ ሕግ መሰረት የተቋቋመ ወይም በፌደራል ወይም በክልል መንግሥታት መዋቅር ውስጥ በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ ወይም ዋነኛ የፋይናንስ ምንጩን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከእነዚሁ አካላት የሚያገኝ ወይም ተጠሪነቱ ለፌደራል ወይም ለክልል መንግሥት የሆነ ማንኛውም አካል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

36) "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል፤

37) "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## 3. ስለፆታ አገላለጽ

የቃሉ አገባብ በሌላ አኳኋን የሚያመለክት ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ በሴት ፆታ የተደነገገው ለወንድም ፆታ ያገለግላል።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡-

Preliminary Draft

1) በዚህ አዋጅ መሰረት በሚቋቋሙና እንደገና በሚቋቋሙ ነባር የመገናኛ ብዙሃን፤

2) ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና ዋነኛ አትኩሮቱ በሀገር ውስጥ ጉዳዮች ላይ የሆነ ማንኛውም በውጭ ሀገር በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት፤

3) ማንኛውም በውጭ አገር ተቋቁሞ እና በውጭ አገር የብሮድካስት ፈቃድ አግኝቶ ማንኛውንም የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ በመጠቀም ፕሮግራሞቹን የሚያሠራጭ፣ በኢትዮጵያ ላይ ያተኮሩ ይዘቶችና አገልግሎቱን ለኢትዮጵያዉያን አድማጭና ተመልካቾች በሃገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚያቀርብ እና/ ወይም ገቢውን በአገር ውስጥ ከሚገኝ የማስታወቂያና የስፖንሰርሽፕ የሚገኝ ሆኖ ሀገር ውስጥ ቅርንጫፍ መ/ቤት ወይም ወኪል ያለው፤

4) በኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ሳይከፍቱ ወይም ወኪል ሳይኖራቸው ቢመዘገቡም ባይመዘገቡም ወይም ፈቃድ ቢያገኙም ባያገኙም ከዉጭ አገር የሚያሰራጩ ማንኛውንም የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ በመጠቀም ፕሮግራሞቹን የሚያሠራጭ፣ በኢትዮጵያ ላይ ያተኮሩ ይዘቶችና አገልግሎቱን ለኢትዮጵያዉያን አድማጭና ተመልካቾች በሃገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚያቀርብ እና/ ወይም ገቢውን በአገር ውስጥ ከሚገኝ ማስታወቂያና ስፖንሰርሽፕ የሚያገኝ፤

5) ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ) መፅሐፍት፤

ለ) ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን፤

ሐ) በየጊዜዉ የሚወጣዉ የኅትመት አካል እስካልሆኑ ድረስ ፎቶ፣ ሥዕልና ካርቱን፤

Preliminary Draft

**ክፍል ሁለት**

የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

## 5. መቋቋም እና ተጠሪነት

1) የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ “ባለሥልጣን” እየተባለ የሚጠራው) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2) የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

3) የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በአገሪቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## 6. ዓላማ

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1) በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤

2) የሕዝብ ጥቅምን ባከበረ መልኩ የሚንቀሳቀሱ መገናኛ ብዙሃን የሚመሩበት የሕግ ማዕቀፍ እንዲፈጠርና እንዲጎለብት የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤

3) የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን በሕግ መሰረት ስራቸውን ማከናወናቸውን መቆጣጠር፤

4) የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሒደቱ ላይ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ መገናኛ ብዙሃን እንዲጠናከሩ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤

Preliminary Draft

5) የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በመደኛነት የሚወያዩበትን መድረክ ማመቻቸትን ጨምሮ በመገናኛ ብዙሃንና በመንግሥት አካላት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖርና እንዲጠናከር የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤

6) ለመገናኛ ብዙሃን የርስ በርስ ቁጥጥርና አስተዳደር ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤

7) የብርድካስት አገልግሎቶች የዜና፣ የአመለካከትና የመረጃ ብዝሃነት እንዲሁም አማራጭ አዝናኝና አስተማሪ ፕሮግራሞች እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤

8) ኢትዮጵያዊያን ዘመናዊ የመገናኛ ብዙሃን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ እገዛና ድጋፍ መስጠት፤ እንዲሁም የብሮድካስት አገልግሎቶች አለም አቀፋዊ የቴክኒክ ደረጃዎችን ማሟላታቸውንና የብሮድካስት ሥርዓቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የወለዳቸው አዳዲስ ግኝቶችን የሚቀበል መሆኑን ማረጋገጥ፤

9) የሕዝብ፣ የንግድና የማኅበረሰብ የብሮድካስት አገልግሎት ፍትሐዊ እድገት እንዲኖር እገዛና ድጋፍ መስጠት፤

10) የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ኢንቨስትመንትና ሃገር በቀልና አዲስ ይዘት ያላቸው ፕሮግራሞች እንዲስፋፉ ማበረታታት፤

11) በብሮድካስት አገልግሎት ተጠቃሚነት፣ ባለቤትነት፣ አመራር፣ ዝግጅትና ስርጭት ላይ የመንግሥትም ሆነ የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል የበላይነት እንዳይኖረው መከልከሉን ማረጋገጥ፡፡

## 7. ሥልጣንና ተግባራት

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

Preliminary Draft

1) የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ ሁኔታን ይወስናል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤ ያድሳል፤

2) በብሮድካስት አገልግሎት ለመሰማራት የሚያስችል የብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ በማዘጋጀት በቦርድ ያስወስናል፡፡ በመመሪያው መሰረትም የብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

3) በየጊዜው የሚወጡ የኅትመት ሥራዎችን በመመዝገብ ሕጋዊ እውቅና ይሰጣል፤

4) የኅትመት ምዝገባ፣ የብሮድካስት ፈቃድ እና ማሳደሻ እና የብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ አገልግሎቶች ክፍያዎችን በመንግሥት በሚያጸድቀው ተመን መሠረት ይሰበስባል፤

5) የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ድንብና መመሪያ አማካይነት ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

6) በማስታወቂያ ሕግ መሰረት ማስታወቂያን ይቆጣጠራል፤

7) የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ በባለፈቃዶች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እንዲሁም በባለፈቃዶች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

8) ስለመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ዕድገትና መሻሻል ጥናት ያደርጋል፤ ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎችን አጠናክሮ ይይዛል፤ በመገናኛ ብዙሃንና በመንግሥት አካላት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችሉ ተግባራትና መድረኮችን ያመቻቻል፤

9) የመገናኛ ብዙሃንን አቅም ለማሳደግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ ይሰጣል፤ የመገናኛ ብዙሃን የራስ ቁጥጥርና አስተዳደር እንዲጠናከር ድጋፍ ያደርጋል፤

10) አግባብነት ያላቸው ሕጎችና የመንግሥት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው መገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት መንግሥትን በመወከል በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤

Preliminary Draft

ከዘርፉ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የመንግሥት ውሳኔዎች ከአለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፤

11) የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል።

## 8. የባለሥልጣኑ ገለልተኝነትና ነፃነት

ባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነቱን ሲወጣ ከማንኛውም ዓይነት አግባብነት ከሌላቸውና ከተቋሙ ዓላማዎች ጋር ከማይሄዱ ፍላጎቶችና ተፅዕኖዎች ገለልተኛና ነፃ መሆን አለበት።

## 9. የባለሥልጣኑ አደረጃጀት

ባለሥልጣኑ፣

1) ቦርድ፤

2) ዋና ዳይሬክተር እና አንድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤

3) ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል።

## 10. ስለቦርድ አባላት

1) ቦርዱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰየሙ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል።

2) የቦርድ አባላት እጩዎችን የመመልመሉና የማፅደቁ ሒደት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን ያለበት ሲሆን በሒደቱም፡-

Preliminary Draft

ሀ) በመገናኛ ብዙሃን ላይ ፍላጎት ያላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እጩ ለመጠቆም እድል እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

ለ) የዚህን አዋጅ ዓላማዎችና መርሆች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተመረጡ እጩዎች ዝርዝር ታትሞ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፤

ሐ) ዜጎች በእጩዎች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ እድል እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

መ) የእጩዎች ምልመላ የኢትዮጵያን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ፆታንና ክልሎችን ያማከለ ፍትሐዊ ውክልና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

3) ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት የቦርዱ አባላት መካከል አንዱን በሰብሳቢነት ሌላኛውን ደግሞ በምክትል ሰብሳቢነት ይሰይማሉ፡፡ ሰብሳቢውና ምክትል ሰብሳቢው ተቃራኒ ፆታ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (3) የተጠቀሰው ምክትል ሰብሳቢ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ኃላፊነቶቹን ለመወጣት በማይችልበት ሁኔታ ሲገኝ ሰብሳቢውን በመተካት የሰብሳቢውን ሥልጣንና ተግባራት ተፈፃሚ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

5) ከቦርዱ አባላት መካከል አምስቱ ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ከመገናኛ ብዙሃን እና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ ተቋማትና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ መሆን አለባቸው፡፡ አራቱ ደግሞ ከመንግሥት አካላት የተውጣጡ ይሆናሉ፡፡

6) አባላቱ ስራቸውን በተገቢው መንገድ እንዲፈፅሙ የሚያስችል ከዘርፉ ጋር የተገናኘ የትምህርት ዝግጅትና ብቃት ወይም ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

7) የቦርዱ አባላት ስራቸውን ሲያከናውኑ ገለልተኛ መሆን አለባቸው፡፡

Preliminary Draft

8) የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ያለድምፅ የሚሳተፍ የቦርዱ አባል እና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

## 11. ለቦርዱ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች

1) ቦርዱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ለቦርድ አባላት የሚከፈለውን ክፍያ መጠን ይወስናል፡፡
2) በቦርድ ስብሰባ ላይ ለመገኘትና ተለይቶ የተሰጠውን ሥራ ለመወጣት አንድ አባል ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሚደረግ ማካካሻ እንደ ክፍያ አይቆጠርም፡፡

## 12. የቦርድ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት

ማንኛውም ለቦርድ አባልነት የሚመረጥ ሰው፡-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለውና በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ኗሪ የሆነ፤

ለ) መልካም ሥነ-ምግባር እና ስብዕና ያለው፣

ሐ) ተግባራቱን በኃላፊነት ለመወጣት ብቃትና ፍላጎት ያለው፤

መ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የአእምሮ በሽታ እንዳለበት ያልታወጀበት፤

ሠ) ከምርጫው ቀደም ብሎ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ በዚህ አዋጅ ክትትልና እርምጃ በሚወሰድበት የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ጋር በተገናኘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት የሌለው፤

ረ) የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊ ወይም ተቀጣሪ ያልሆነ፤

ሰ) ከመንግሥታዊ የኃላፊነት ቦታ ሥልጣኑን አለአግባብ በመጠቀሙ የተከሰሰና የተፈረደበት፣ እንዲሁም በፍርድ ቤት የሲቪል መብቱ የተገፈፈ በመሆኑ የተነሳ ከኃላፊነቱ ተገዶ ያልለቀቀ ወይም ያልተባረረ፤

Preliminary Draft

መሆን አለበት።

## 13. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የዚህን አዋጅ አፈጻጸምና የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፤
2) የባለሥልጣኑን የሥራ እቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ ይገመግማል፤
3) የባለሥልጣኑን የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ እንዲሁም የደሞዝ፣ የአበል እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች መመሪያ አዘጋጅቶ ከአስተያየት ጋር ለመንግሥት ውሳኔ ያቀርባል፤
4) የባለስልጣኑን ውሳኔዎች በይግባኝ ይመለከታል። አመልካቾች እና ባለፈቃዶች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች፤ ባለፈቃዶችን አስመልክቶ ከሕዝብ የቀረቡ ቅሬታዎችን እና የዚህን አዋጅ አፈጻጸም በሚመለከት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤
5) ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ ያፀድቃል፤
6) የዚህን አዋጅ አፈጻጸም በሚመለከት በሚቀርቡ በማናቸውም የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ እንደአግባቡ ለመንግሥት ውሳኔ ያቀርባል።

## 14. የቦርድ ውክልና

Preliminary Draft

1) ቦርዱ በጠቅላላው ወይም በተለየ ጉዳይ ላይ ለማንኛውም የቦርድ ኮሚቴ ወይም አባል፣ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ተወካይ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲያከናውን ውክልና ለመስጠት ሊወስን ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ውክልና መመሪያ ማውጣትንና ይግባኝን መመልከትን አያካትትም፡፡

## 15. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

1) የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፡፡
2) የቦርዱ አምስት አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት ለተጨማሪ የስራ ዘመን እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ አንድ የቦርድ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡
3) በተለያዩ ምክንያቶች የቦርድ አባላት በቋሚነት የተጓደሉ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ተተኪ አባላትን ያሾማሉ፡፡ የተተኪ አባላት የስራ ዘመን የተተኩበት ቦርድ የስራ ዘመን ይሆናል፡፡

## 16. የቦርድ አባላት ከአባልነት የሚነሱባቸው ሁኔታዎች

1) አንድ የቦርድ አባል የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

   ሀ) በፈቃዱ መልቀቅ እንደሚፈልግ ለቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በጽሑፍ በማስታወቅ ሲለቅ፤

   ለ) ህይወቱ ሲያልፍ፤

   ሐ) ከኃላፊነቱ በሚከተሉት ምክንያቶች ሲነሳ፡-

Preliminary Draft

1) ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ጉድለት ሲያሳይ፤

2) በአካላዊ ወይም አእምሯዊ ህመም ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ካልቻለ፤

3) ያለ በቂ ምክንያት እና ሳያሳውቅ በተከታታይ አምስት ጊዜ ስብሰባ ከቀረ ወይም በዓመት ዉስጥ ከተደረጉት ስብሰባዎች ከግማሽ በላይ በሚሆኑት ካልተገኘ፤

4) የዚህን አዋጅ የጥቅም ግጭት ድንጋጌዎች እያወቀ ጥሰት ከፈጸመ፡፡

2) አንድ የቦርድ አባል ለመነሳት በቂ ምክንያቶች መሟላታቸውን ቦርዱ በአብላጫ ድምጽ ከወሰነ፣ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ጸሐፊ አማካኝነት ዉሳኔዉን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በማሳወቅ  ከኃላፊነት እንዲነሳ ያደርጋል፡፡

3) ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርድ አባላት ስለመነሳታቸውና ስለተነሱበት ምክንያት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

4) ማንኛውም የቦርድ አባል ከኃላፊነቱ እንዲነሣ በመደረጉ ምክንያት የአባላት መጓደል በሚፈጠርበት ጊዜ በአንቀጽ 15 ንዑስ-አንቀፅ (3) መሰረት እንዲተካ ይደረጋል፡፡

**17. የቦርድ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

1) ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ወይም ሦስት ቦርድ አባላት ስብሰባ እንዲጠራ ከወሰኑ፣ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቦርድ መወሰን ያለባቸዉ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

2) በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3) የቦርዱ ውሳኔዎች በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ያልፋሉ፡፡

4) የስብሰባው ቃለ-ጉባዔ ሊያዝና ሊቀመጥ ይገባል፡፡

Preliminary Draft

5) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 18. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት

1) የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማል፡፡

2) ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን በዚህ አዋጅና ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለሥልጣኑን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ መርሐ ግብርና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው የሥራ መርሐ ግብርና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤



Preliminary Draft

ሰ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

4) ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 19. የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባራት

1) የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሮች በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በቦርዱ ይሾማሉ፡፡

2) ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣

ሀ) ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት በሥራቸው የተመደቡ የሥራ ዘርፎችን ይመራሉ፤ ያስተባብራሉ፤

ለ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ፡፡

3) ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሰራል፡፡

## 20. ስለ የባለሥልጣኑ የጥቅም ግጭት መርህ

1) በማናቸውም ሁኔታ እንኳን ቢሆን ዋና ዳይሬክተሩ፣ ማንኛውም የቦርድ አባል፣ ወይም ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚቆጣጠረው ማንኛውም ኩባንያ ላይ ቀጥተኛ የባለቤትነት ጥቅም ሊኖረው አይችልም፡፡

Preliminary Draft

2) ከባለሥልጣኑ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ዋና ዳይሬክተሩም ሆነ የቦርድ አባል፣ ወይም ማንኛውም የባለስልጣኑ ሰራተኛ በራሱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ መሠማራት አይችልም፡-

   ሀ) የራሱን የግል የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

   ለ) የባለቤቱን ወይም ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጁን የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

   ሐ) የራሱን የንግድ አጋር የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

   መ) በኦፊሰርነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በአጋርነት፣ በሰራተኝነት ወይም በባለአደራነት የሚያገለግለውን የማንኛውም ተቋም የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤ ወይም፣

   ሠ) በሥራ ለተቀጠረበት ወይም ለሥራ ቅጥር በድርድር ላይ የሚገኝበትን ከማንኛውም አካል የፋይናንስ ጥቅም ጋር በሚገናኝ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) የተገለጹት ሁኔታዎች ሲኖሩ የባለስልጣኑ አባላት እንዲሁም ዳይሬክተር እና ምክትሎች ለቦርዱ፣ ሰራተኞች ደግሞ ለዋና ዳይሬክተሩ ለጥቅም ግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል ያሉትን ነገር የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ የቦርድ አባላቱ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ መክረው አባሉ በስብሰባ እንዳይሳተፍ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ የተቀሩት አባላት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ የስብሰባው ቃለ-ጉባዔ አካል ሆኖ መመዝገብ አለበት፡፡

4) ይህን የጥቅም ግጭት ድንጋጌ የጣሰ የባለሥልጣኑና የቦርዱ አባል ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡ አባሉ የተሳተፈበት ስብሳባም የጥቅም ግጭት በተነሳበት ጉዳይ ላይ ፈራሽና የማይጸና ነው፡፡

5) የጥቅም ግጭትን የሚተረጉምና ከጥቅም ግጭት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን የሚመለከት መመሪያ ቦርዱ ያወጣል፡፡

## 21. በጀት እና የፋይናንስ አስተዳደር

Preliminary Draft

1) የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

ሀ) በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤

ለ) በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ከሚሰበሰቡ የፈቃድና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች፤

ሐ) ዘርፉን ለማሳደግና ለማጎልበት ፕሮጀክት በመቅረፅና በቦርዱ በማስፀደቅ ከሚገኙ እርዳታና ድጋፍ ምንጮች፡፡

2) የባለስልጣኑ የፋይናንስ አስተዳደር የሚመራው በሚመለከተው የፌደራል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

### 22. ስለሂሳብ መዛግብት

1) ባለሥልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2) የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት፣ ምዝገባ እና ፍቃድ

### 23. መሰረታዊ መርሆዎች

1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው ግልፅ በሆነ መስፈርትና ያለአድልኦ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት የማቋቋምና የሕግ ሰውነት ያለው ሰው የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

Preliminary Draft

2) ማንኛውም በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ለማቋቋምና የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት ወይም ለማሳደስ አመልክቶ ባለሥልጣኑ የከለከለ አካል በውሳኔው ላይ ለቦርዱ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ የቦርዱን ውሳኔም በመቃወም ለፍርድ ቤቶች በማመልከት ፍትሕ ማግኘት ይችላል፡፡

3) የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት ድንጋጌዎች መውጣት ያለባቸው ጠቅላይነትን ለመከላከልና የሃሳብ ብዝሃነትን እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡

4) ዴሞክራሲ በአግባቡ እንዲሰራ አስቻይ የሆነ ክርክር ለማድረግና ለአንባብያን፣ ለአድማጮችና ለተመልካቾች ተደራሽ የሆኑ ሰፊ የዜናና የመረጃ ምንጭ የሚሆኑ ብዝሃነት ያላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡

## 24. የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት

1) ዜጎች በግል ወይም የሰውነት መብት በሕግ በተሰጠው ድርጅት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት በባለቤትነት ለማቋቋም ይችላሉ፡፡

2) የሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም ድርጅት የብሮድካስት አገልግሎት ስራ ባለቤት በመሆን ለመስራት ይችላል፡፡

3) የውጪ ዜጎችና ድርጅቶች እንዲሁም የውጭ ዜጎች ከ25 በመቶ ያልበለጠ የአክሲዮን ድርሻ የያዙባቸው ድርጅቶች በአንድ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት እና የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅት ላይ ከ25 በመቶ ያልበለጠ የባለቤትነት ድርሻ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

Preliminary Draft

**25. የጎንዮሽ ባለቤትነት**

1) ቁጥሩ ከ100,000 በላይ የሆነ የተመዘገበ ነዋሪ ለሚገኝበት አካባቢ ወይም ክልል የብሮድካስት ፈቃድ በያዘ ድርጅት ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከ25 በመቶ በላይ ድርሻ ወይም ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው ተመሳሳይ ፈቃድ በያዘ እና በተመሳሳይ ወይም በተደራራቢ የገበያ አካባቢ የብሮድካስት አገልግሎት ከሚሰጥ ሌላ ድርጅት ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከ25 በመቶ በላይ ድርሻ ወይም ውጤታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም፡፡

2) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በያዘ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው አንድ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ስራን ያለገደብ መስራት ይችላል፡፡ ይሁንና የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በያዘ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው ያለገደብ እንዲሰራ ከተፈቀደለት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት በተጨማሪ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ስራን ከሚሰራ ሌላ ማንኛውም ድርጅት ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከ25 በመቶ በላይ ውጤታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም፡፡

3) በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ስራን የሚሰራ ድርጅት ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው የኅትመት ስራን ከሚሰሩ ሌሎች ድርጅቶች ላይ ያለገደብ የአክሲዮን ድርሻ መግዛት፣ ደርጅቱን መጠቅለልና ውህደት መፍጠር ይችላል፡፡

Preliminary Draft

4) በዚህ አንቀፅ ከንኡስ አንቀፅ 1 እስከ 3 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከተው ውጤታማ ቁጥጥር የሚወሰንበትና የመለኪያ ቅኝቱ የሚከናወንበት ሥነ-ሥርዓት ደንብ እስኪወጣ ድረስ ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር፣ ማንኛውም ኩባንያ ወይም ድርጅት አክስዮኖች ወይም ካፒታል ወይም እሴቶችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በድርጅቱ ወይም በድርጅቶቹ ከ25 በመቶ በላይ የያዘ ማንኛውም ሰው ውጤታማ ቁጥጥር እንዳለው ይገመታል፡፡

5) የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን በየሦስት አመቱ የመገናኛ ብዙሃንን ይዞታ እና የመገናኛ ብዙሃን የገንዘብና የገበያ እንዲሁም የባለቤትነት ይዞታን ከገበያና ከሃሳብ ጠቅላይነት አንጻር በመገምገም በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (1) እስከ (4) የተደነገገው ገደብና የአክስዮን ድርሻ ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 26. የፈቃድ ማስተላለፍ መከልከል

1) አንድ ፈቃድ የሚሰጠው የፈቃዱ አመልካች ተብሎ ለተለየው ሰው በመሆኑ ባለሥልጣኑ አስቀድሞ በፅሁፍ ካላጸደቀው በስተቀር ፈቃድን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ማስተላለፍ የሚከተሉትን ያካትታል፡ -

ሀ) የፈቃድ ቁጥጥር ለውጥ፤

ለ) በፈቃዱ የተሠጡትን መብቶች በፈቃደኝነት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤ እና፣

Preliminary Draft

ሐ) የፈቃድ ሁኔታው ላይ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ለመለወጥ የሚደረግ ማንኛውም ድርጊት፡፡

3) በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ማስተላለፍ ውጤታማ ቁጥጥር የሌለው የአክሲዮን ለውጥን አያመለክትም፡፡

## 27. በየጊዜው የሚወጣ የኅትመት ስራ ምዝገባ

1) በግለሰብ እና ሕጋዊ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት በየጊዜው የሚወጣ የኅትመት ስራ ለመስራት የሚከተሉትን መረጃዎች በማሟላት ለባለሥልጣኑ ሕጋዊ እውቅና እንዲሰጠው ማመልከት ይቻላል፡-

ሀ) የመስራች/ቾች ስምና አድራሻ፤

ለ) የባለቤትነት ሁኔታ፤

ሐ) የዋና አዘጋጅ ስምና አድራሻ፤ እና፣

መ) ንግድ ፈቃድ፡፡

2) ባለሥልጣኑ የምዝገባ ጥያቄ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ምዝገባውን በማከናወን የእውቅና ምስክር ወረቀት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በ30 ቀናት ውስጥ የእውቅና የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡ ለምዝገባ ያመለከተ ግለሰብ ወይም ድርጅት መስፈርቱን አሟልቶ ማመልከቻ ካስገባ 30 ቀን ካለፈው የእውቅና የምስክር ወረቀት እስከሚሰጠው መጠበቅ ሳያስፈልገው ወደ ህትመትና ስርጭት መግባት ይችላል፡፡

3) በየጊዜው የሚወጣ የኅትመት ስራን ማሳተም፡-

ሀ) አስቀድሞ በሕጋዊ መንገድ ለተመዘገበ ማንኛውም ድርጅት እንቅስቃሴዎች አስፈላጊነቱ ተፈጥሯዊ ከሆነ፤ ወይም፣

Preliminary Draft

ለ) መንግሥታዊ አካል ዓላማውን ለማራመድ ወይም በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ካስፈለገው በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

## 28. የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ

1) ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በታገደ ወይም በተሰረዘ ፈቃድ የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችን ተጠቅሞ በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

2) ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርበለት፣ የፈቃድ ጥያቄ አቅራቢው በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ያሟላና በብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ መሰረት መስፈርቱን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ያቀረበው የማሰራጫ መንገድ ውስን ሃብት በመሆኑ የተገደበ ካልሆነ ፈቃዱን በ30 ቀናት ውስጥ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ አመልካቹ ፈቃድ ካልተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

3) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾች በዚህ አዋጅ መሠረት በተለያየ ደረጃ እንዲሞሉ የሚጠበቅባቸውን ፎርም ባለሥልጣኑ በድረ-ገጹ ተደራሽ እንዲሆንና እንዲሞላ በማድረግ አማራጭ መፍጠርና ሒደቱን ማቅለል ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ይህን ማድረግ ያልቻሉ አመልካቾች በአካል አገልግሎቱን ያገኛሉ፡፡

4) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

ለ) የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤ እና

Preliminary Draft

ሐ) የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ።

## 29. የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችና የፈቃድ አይነቶች

1) የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶች ወይም የፈቃድ አይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

ለ) የሳተላይት ኔትወርክ በማቋቋም ወይም ማንኛውንም የሳተላይት ቻናል በመከራየት የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

ሐ) በኬብል አማካይነት የቴሌቪዥን ኘሮግራም በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

መ) የውጪ ኘሮግራሞችን በመቀበል ለደንበኞች በክፍያ የማድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

ሠ) ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶች ፈቃድ።

2) ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቦርድ በማፀደቅ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ በሌሎች ብሮድካስተሮች ያልተሸፈነ ወይም ትኩረት ያልተሠጠበት የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ለሚያመለክት አመልካች ልዩ የሕዝብ፣ የንግድ ወይም የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡ ፡

## 30. የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾችን ስለመጋበዝ

Preliminary Draft

1) ለብሮድካስት አገልግሎት መዋል የሚችል ውስን የሀገር ሀብት የሆነ የአየር ሞገድ መኖሩ ከሚመለከተው ተቋም መረጃ በደረሰው ጊዜ ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾችን ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን በሚገለጽ ማስታወቂያ የመጋበዝ ግደታ ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጣው ማስታወቂያ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) ፈቃድ ለመስጠት የታሰበውን የብሮድካስት አገልግሎት አይነት፤

ለ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል ወይም አካባቢ፤

ሐ) ዝግጁ የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ፤

መ) የፈቃድ ሁኔታዎች፤

ሠ) አንኳር የፎርማት ግዴታዎች፤

ረ) ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

ሰ) የፈቃድ መስፈርቶች፤

ሸ) የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜና ቦታ፤ እና፣

ቀ) የማመልከቻና የፈቃድ ክፍያ መጠን፡፡

3) ፍትሐዊና አወዳዳሪ ሒዴት ለማረጋገጥ አዳዲስ ፈቃዶች ሁልጊዜም ቢሆን ማስታወቂያ ሊወጣባቸው ይገባል፡፡

4) በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት በሚወጣው ማስታወቂያ በሚጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

Preliminary Draft

5) ለራዲዮና ለቴሌቪዥን አመልካቾች እንደየ ቅደም ተከተላቸው ማመልከቻቸውን ለማዘጋጀት የሦስትና የዘጠኝ ወራት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## 31. የፈቃድ ማመልከቻ ሒዴት

1) ባለሥልጣኑ በፈቃድ አመልካቾች የሚሞላ የማመልከቻ ቅጽ ማዘጋጀት አለበት፡፡

2) በማስታወቂያ ለተደረገው ጥሪ ምላሽ የሚሰጡ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾችን በፍትሐዊነት ለማስተናገድ ተመሳሳይና በቂ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ ማመልከቻዎችን ለመገምገም አስፈላጊ ነው የሚለውን ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ አመልካቾችን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 32. የፈቃድ ሁኔታዎች

1) ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው የገለጻቸው እንዲሁም በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በፈቃዱ ውስጥ የተመለከቱት ሁኔታዎች የፈቃዱ ግዴታዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡

2) ማንኛውም የብሮድካስት ፈቃድ የሚከተሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ያካትታል፡-

ሀ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል ወይም አካባቢ፤

ለ) የቴክኒክ መስፈርቶች፤

ሐ) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ሥርጭት የሚጀምርበት ጊዜና ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

Preliminary Draft

መ) የፈቃድ ማደሻ ሁኔታዎች፤

ሠ) አዲስ ፈቃድ ለመስጠትና ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስፈልግ ወጪ ለመሸፈን በየአመቱ የሚከፈል ክፍያ መጠን፤

ረ) የፕሮግራም ፎርማት ግዴታዎች፤

ሰ) የፕሮግራም የይዘት ደረጃዎች፤

ሸ) የፈቃድ ሁኔታዎች ሲጣሱ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች፤

ቀ) ባለሥልጣኑ በመደበኛነትና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸው የመረጃ አይነቶች፤ እና፣

በ) ፈቃድ የሚታደስባቸው ሁኔታዎች።

## 33. የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች

1) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው አመልካቹ በዚህ አዋጅና አዋጁን መሰረት አድርጎ በወጣ መመሪያ የተደነገጉትን መስፈርቶች ሲያሟላ ይሆናል።

2) ባለሥልጣኑ የአመልካቾችን ብቃት ለመመዘን የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት ያወጣል። በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀው መስፈርት የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፦

ሀ) ከብሮድካስቲንግ ቴክኖሎጂ እድገቶች ጋር በተያያዘ ሊሰጥ ከታሰበው አገልግሎት የሚጠበቅ የቴክኒክ ጥራትና አመልካቹ በፕሮጀክት ሀሳብ-ሥራው የዘረዘራቸው መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤



Preliminary Draft

ለ) አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ተስማሚነት፣ ድርጅታዊ ብቃት፣ የሥራ ልምድና ሙያዊ እውቀት፤

ሐ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቅምና ምንጭ፣ አስተማማኝነትና ሥራውን ለማስኬድ ያለው ዝግጁነት፤

መ) በአመልካቹ ፕሮጀክት ሀሳበ-ሥራ በአመልካቹ የቀረቡት ፕሮግራሞች ይዘትና በፕሮግራሞቹ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶች፤ እና፣

ሠ) አመልካቹ ለአገልግሎቱ የመደበው የስርጭት ጊዜ።

Draft

## 34. በፈቃድ ላይ የሚሠጥ ሕዝባዊ አስተያየት

1) ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ለመገምገም ጠቃሚ መስሎ ከታየው ባለሥልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ ሊጠራ ይችላል።
2) ባለሥልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚፈልጉ ጉዳዮችን ለይቶ ማውጣት አለበት።
3) ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበት ቦታ የብሮድካስት አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢ ወይም ጣቢያው በሚገኝበት ክልል የሚገኝ መሆን አለበት።
4) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሻለ ሆኖ ካገኘው ሕዝባዊ አስተያየቱ ወይም የተወሰነው ክፍል በዝግ እንድካሄድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

## 35. ተቀባይነት ስለሌለው ማመልከቻ

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ማመልከቻው ዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልገው ውድቅ በማድረግ በጽሁፍ እንዲያውቀው የሚደረገው አመልካቹ፦

ሀ) የፋይናንስ አቅሙንና ምንጩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ ካላቀረበ፤

ለ) ዝርዝር የኘሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፤ ወይም፣

ሐ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 37 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል ከሆነ ነው።

## 36. የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ስለማይሰጣቸው ሰዎች

1) የሚከተሉት ሰዎች ውስን የሀገር ሀብት የሆነ የአየር/የሬዲዮ ሞገድ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም፡-

ሀ) በውጭ አገር ዜጎች የተቋቋመ ወይም የውጪ አገር ዜጋ በካፒታሉ ከ25 በመቶ በላይ የአክስዮን ባለድርሻ የሆነበት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፤

ለ) የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅት ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ባለአክሲዮን የሆነበት ወይም የፖለቲካ ድርጅት የበላይ አመራር አባል ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ባለአክሲዮን ወይም በማንኛውም ደረጃ የአመራር አባል የሆነበት ድርጅት፤

ሐ) የኃይማኖት ድርጅት፤

2) የሚከተሉት ሰዎች ውስን የሀገር ሀብት ከሆነው የአየር/የሬዲዮ ሞገድ ውጭ የሆኑ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች ሊሰጣቸው ይችላል፡-

ሀ) በውጭ አገር ዜጎች የተቋቋመ ወይም የውጪ አገር ዜጎች በካፒታሉ ላይ የአክስዮን ባለድርሻ የሆኑበት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፤

ለ) የኃይማኖት ድርጅት፤

3) የሚከተሉት ሰዎች ምንም አይነት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም፡-

Preliminary Draft

ሀ) የፖለቲካ ፓርቲዎች፤

ለ) በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሲቪል ወይም ከፖለቲካ መብቶቹ የታገደ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሕግ ችሎታውን ያጣ ሰው፡፡

## 37. የውሳኔ አሰጣጥ

1) ባለሥልጣኑ ፈቃድ በመስጠት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚከተሉትን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ) በፅሁፍ በቀረበው ማመልከቻ የተገኘውን መረጃ በመገምገም፣ ሕዝባዊ አስተያየት የማይሰጥ ከሆነ በፅሁፍ የቀረበለትን ማንኛውም ማስረጃ፤

ለ) በሕዝባዊ አስተያየት መድረኩና ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያት የቀረቡትን የቃልና የፅሁፍ ማስረጃዎችን ጨምሮ የሕዝባዊ አስተያየቱ ውጤት፤ እና፣

ሐ) ከሕዝባዊ አስተያየት ውጭ የተገኘ ማንኛውም አይነት መረጃ፡፡

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመር በአንቀጽ 33 የተመለከቱ መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ወይም ተቀባይነት የሌለው ከሆነ በአንቀጽ 35 መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3) የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ ወይም ፈቃድ እንዳይሰጥ ባለሥልጣኑ የሚወስን ከሆነ ምክንያቱን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

4) ፈቃድ የተከለከለ ማንኛውም አመልካች ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፤ ቦርዱም አቤቱታው በደረሰው

Preliminary Draft

በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት። በቦርዱ ውሳኔ ያልተስማማ አመልካች ቅሬታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል።

5) የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ስምምነት በመፈረምና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ በመፈጸም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

## 38. የማስፋፊያ ፈቃድ

1) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ እንደአግባብነቱ፡-

ሀ) ተጨማሪ ሥርጭት ለማካሔድ የጣቢያውን አቅም ለማሳደግ ወይም የማሠራጫ መሣሪያውን አቅም ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግ ከፈለገ፤

ለ) የማሠራጫ መሣሪያውን ጉልበት ከተፈቀደው መጠን ለመለወጥ ወይም ቦታ ለመቀየር ከፈለገ፤

ሐ) የአንቴናውን ዓይነትና የአንቴና ተሸካሚ ምሰሶውን ርዝመት ለመለወጥ ወይም ቦታ ለመቀየር ከፈለገ፤ ወይም፣

መ) ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ ለማግኘት ከፈለገ፤

ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

2) በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰውን መስፈርት ለማሟላት ሲባል የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ቀደም ብሎ ፈቃድ በወሰደበት የሬዲዮ ሞገድ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፈቃድ ሲጠይቅ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡

-

ሀ) የተመረጠው ማስፋፊያ ቦታ ለታቀደው አገልግሎት ብቁ መሆኑን፤

Preliminary Draft

ለ) የብሮድካስት አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረቡት መሣሪያዎች ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ ዕቅድ ጋር መጣጣማቸውን፤

ሐ) የሌላ የመገናኛ መሣሪያ አገልግሎት አሰጣጥን የማያውክ መሆኑን፤

መ) ፈቃድ በተጠየቀበት አካባቢ የተመዘገበ የሬዲዮ ሞገድ መኖር አለመኖሩን፤

ሠ) የማስፋፊያ ፈቃድ የተጠየቀበት ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ በሌላ የብሮድካስት አገልግሎት አለመያዙን ወይም ለሌላ አገልግሎት አለመፈለጉን፤ እና፣

ረ) ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ ኅብረተሰብ ፍላጎት፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የማስፋፊያ ፈቃድ የተሰጠው ባለፈቃድ መሣሪያው የሚተከልበትን ቦታ ከአስፈላጊ ዝርዝር መረጃ ጋር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

### 39. የብሮድካስት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን

1) ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለ10 ዓመት ጸንቶ የሚቆይ ይሆናል።

2) ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራጭ ሲሆን ለ8 ዓመት፤

ለ) የሥርጭት ሽፋኑ በክልል ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለ10 ዓመት፤

ሐ) የሥርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ከሆነ ለ12 ዓመት፤

መ) የሥርጭት ሽፋኑ በአዲስ አበባና አካባቢዋ የተወሰነ ከሆነ ለ6 ዓመት፤

ሠ) መደበኛ የማኅበረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ ለ5 ዓመት፤



Preliminary Draft

ረ) የአጭር ጊዜ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ ለ1 ዓመት፡፡

## 40. የብሮድካስት ፈቃድን ስለማሳደስ

1) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39 የተወሰነው የፈቃድ ዘመን የጊዜ ገደብ ከማለቁ ከአንድ ዓመት ባልበለጠና ከስድስት ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማደሻ ቅጽ ሞልቶ የዕድሳት ማመልከቻውን በማቅረብ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች የብሮድካስት ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻን ይቀበላል፡-

   ሀ) አመልካቹ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በሥራ ላይ ባለው ፈቃድ የተዘረዘሩትን የፈቃድ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን ያከበረ ከሆነ፤

   ለ) አመልካቹ ፈቃድ ቢታደስለት ፈቃድ ሁኔታዎችን ያከብራል ብሎ ካመነ፤

   ሐ) ፈቃዱ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ባለፈቃዱ የሰጠው አገልግሎት በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ከሆነና ተደጋጋሚ ቅሬታ እንዳልቀረበበት የኋላ ታሪኩ መዝገብ የማያሳይ ከሆነ፤ እና

   መ) ፈቃዱን ለሌላ አመልካች ለመስጠት ምንም አይነት አስገዳጅ ምክንያት የሌለ ሲሆን፡፡

3) ባለሥልጣኑ በፈቃድ ማደስ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ፈቃዱ እንደጸና ይቀጥላል፡፡

Preliminary Draft

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የታደሰ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 39 በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

5) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ በንዑስ-አንቀፅ (4) የተመለከተውን የታደሰ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበትን ዘመን ለማሳጠር ምክንያቶቹን በመዘርዘር ፈቃዱን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

6) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ላለማደስ የሚይስችሉ ምክንያቶች ካገኘ የውሳኔውን ምክንያቶች ለባለፈቃዱ በመግለፅ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ በውሳኔው ላይ አስተያየት እንዲሰጥና ተቃውሞ ካለው የፅሁፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጥ ይገባል፡፡

7) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት የባለፈቃዱን ምላሽ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

8) ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ላለማደስ ሃሳብ ካለው ከ30 ቀናት ያላነሰ አስቀድሞ ለባለፈቃዱ ማስታወቅ አለበት፡፡

## 41. የብሮድካስት ፈቃድን ስለማሻሻል

1) ባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድን በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊያሻሽል ይችላል፡-

ሀ) ማሻሻያው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚፈጸም ከሆነ፤

ለ) በአዋጁ ላይ ለውጥ ከተደረገና በባለሥልጣኑና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኮሚሽኑ ላይ የተጣለው አለም አቀፍ ግዴታ አፈፃፀም ማሻሻያ የሚጠይቅ ከሆነ፤ እና፣

ሐ) ባለሥልጣኑ የሕዝብን ጥቅም ለማስከበርና የአዋጁን ዓላማዎች ለመፈጸም ማሻሻያው አስፈላጊ ነው ብሎ ሲወስን፡፡

2) ባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድን ለማሻሻል ሲወስን ለብሮድካስት ባለፈቃዱ አስቀድሞ ማስታወቅ አለበት፡፡ ማስታወቂያው የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፡-

Preliminary Draft

ሀ) የማሻሻያውን ዝርዝር፤

ለ) ለማሻሻል ያስፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት፤ እና፣

ሐ) ማሻሻያው ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ።

3) የብሮድካስት ባለፈቃዱ በማሻሻያው ላይ ለባለሥልጣኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ በቂ እድል ሊሰጠው ይገባል።

4) ማሻሻያው የተፈለገው ከራዲዮ ሞገድ አስተዳደር ጋር በተገናኘ ከሆነ በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጁ (ረቂቅ) መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

**42. የፈቃድ፣ ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ**

1) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፈቃድ ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ መክፈል አለበት።

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንዲሁም ሌላ ለባለሥልጣኑ መከፈል ያለበትን የክፍያ መጠን በየጊዜው እያጠና በመንግሥት ያስወስናል።

3) ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያው የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ መከፈል አለበት፤ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፈላል፤ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከአመታዊ ክፍያ ወይም የፈቃድ ማደሻ ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

Preliminary Draft

## ክፍል አራት

## የመገናኛ ብዙሃን መብቶች እና ግዴታዎች

### 43. መሠረታዊ መርሆዎች

1) በግልፅ የተደነገጉ ሕጎች ከሌሉ በስተቀር የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የሚስተጓጉሉ ማናቸውም አሰራሮች፣ አስተዳደራዊ ተግባራትና እርምጃዎች ተከልክለዋል።

2) የመገናኛ ብዙሃን ሕጋዊ ግዴታቸውን በማክበር ኃላፊነት በተሞላው ሁኔታ ሙያው በሚስፈልገው ብቃትና በከፍተኛ ሥነ-ምግባር ተግባራቸውን እንዲያከናውኑና፤ ነፃና ዘርፈ ብዙ የሆነ፣ ሰፊና የተለያየ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበት ምህዳር በመፍጠር ለሃሳብ ልውውጥ መጎልበት አስተዋፅዎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

### 44. የመገናኛ ብዙሃን መብቶች

1) ማንኛቸውም የመገናኛ ብዙሃን አካላት ሕዝባዊ ተግባራቸውን ለመወጣት፡-

ሀ/ ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፤

ለ/ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብ፤

ሐ/ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን፣ መሣሪያዎችን የመጠቀም፤ ወይም፣

መ/ የተለያዩ ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሒደት የመሳተፍ መብት አላቸው።

2) መገናኛ ብዙኃን በመረጡት መንገድ የመደራጀት መብት አላቸው።

3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት መብቶች የመገናኛ ብዙኃን አካል ለሆኑ ጋዜጠኞች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

Preliminary Draft

**45. ምንጭን ለመግለጽ ያለመገደድ ጥበቃ**

1) ጋዜጠኞች ማንኛውም ሰው ለመገናኛ ብዙሃን ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ሁኔታዎች መረጃ ለማግኘት የመረጃ ምንጭ እንዲገለጽ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) የተፈጸመ ከባድ ወንጀል ላይ ክስ ለመመስረት ወይም መከላከያ ለማቅረብ ወይም በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱና በሃገር ጸጥታ ላይ ግልጽና ድርስ አደጋን ለመከላከል ወሳኝ የመረጃ ምንጭ ሲሆን፤ እና፣

ለ) ክስ ለመመስረት ወይም መከላከያ ለማቅረብ አስፈላጊና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ከሆነ እና ድርስ የሆነውን አደጋ ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለ ሲሆን፡፡

3) በፍርድ ቤት የተሰጠውን የመረጃ ምንጭ የመግለፅ ግዴታ ባለመቀበል ምንጫቸውን ላለመግለጽ የሚወስኑ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የፍርድ ቤት ትእዛዝን ባለማክበርና ከገንዘብ ቅጣት በዘለለ ቅጣት ሊጣልባቸው አይገባም፡፡

**46. የእርማት ወይም መልስ የመስጠት መብት**

1) በመገናኛ ብዙሃን በቀረበ የፍሬ ነገር ዘገባ መልካም ስሙና ክብሩ በሐሰት ወይም በአሉታዊ ጎኑ ተጎዳብኝ ያለ ማንኛውም ሰው ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ላይ ያለ ክፍያ እርማት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

2) ማንኛውም ግለሰብ የራሱን መልካም ስምና ክብር የመከላከል የሲቪል መብትን የጣሰ መረጃ በመገናኛ ብዙሃን ከቀረበ ግለሰቡ ለዚህ መረጃ የሰጠው ምላሽ ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ላይ ያለ ክፍያ እንዲካተት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

Preliminary Draft

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተደነገጉት መብቶች ተግባራዊ የሚደረጉት በሚከተሉት ደንቦች አማካይነት ነው፡-

ሀ) በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት በሚሆንበት ጊዜ በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ከሆነ እርማቱ ወይም ምላሹ በተላከ በ24 ሰዓት ውስጥ፣ ዕለታዊ ጋዜጣ ከሆነ በሦሥት ቀናት ውስጥ፣ ሳምንታዊ ጋዜጣ ከሆነ በሰባት ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ አይነት ኅትመት ከሆነ በቀጣዩ እትም መውጣት አለበት፡፡

ለ) የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮ ፕሮግራም በሚሆንበት ጊዜ እርማቱ ወይም ምላሹ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ መተላለፍ አለበት፡፡

ሐ) መገናኛ ብዙሃኑ ለእርማት ወይም ማስተባበያ የሚቀርበው መልስ ከዘገባው ጋር የተያያዘ፣ ተመጣጣኝና ሕጋዊ ይዘት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ መልስ የመስጠት መብት በፍሬ ሃሳብ እውነተኛነት ላይ የተረጋገጠን ዘገባ በሐሰት ለማስተባበል ሊውል አይገባም፡፡

መ) ዘገባው የተሰራጨው ምርጫ በሚካሔድበት ወቅት ከሆነና ከምርጫ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ብቻ በዚህ ንኡስ አንቀፅ 1 (ሀ) እና (ለ) የተጠቀሰው የሦሥት ቀን የጊዜ ወደ 24 ሰአት፣ የአምስት ቀኑ ገደብ ደግሞ ወደ 48 ሰዓት ዝቅ እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

ሠ) እርማቱ ወይም ምላሹ እንዲወጣ ከተጠየቀ በኋላ ኅትመቱ ከተቋረጠ ጥያቄው የቀረበለት መገናኛ ብዙሃን ክፍያዉን በመሸፈን በሌላ ተመሳሳይ መገናኛ ብዙሃን ላይ እርማቱን ወይም ምላሹን እንዲያወጣ ይደረጋል፡፡

ረ) የዚህ ንኡስ አንቀፅ 1 (መ) ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው ምላሹ ለመገናኛ ብዙሃኑ የደረሰው ምላሹ የሚወጣበት ኅትመት ወይም ፕሮግራም ለመታተም ከመላኩ ወይም በአየር ከመለቀቁ ስድስት ሰዓታት ቀደም ብሎ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ከስድስት ሰዓታት ቀደም ብሎ ካልደረሰ በቀጣዩ አጋጣሚ መካተት ይኖርበታል፡፡

Preliminary Draft

4) መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ማንኛውም ሰው የኅትመቱ ወይም የፕሮግራሙ አዘጋጅ ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ለማመልከት ይችላል፡፡

5) ማመልከቻው የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔውን በ10 ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም በምርጫ ወቅት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻው በቀረበለት በ24 ሰዓት ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

6) ኃላፊ የሆነው ሰው መልሱን ለማውጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን ከተረዳ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡

7) የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2049 የተመለከቱትን ከተፈጻሚነት አያስቀሩም፡፡

8) በዚህ አንቀፅ ከንኡስ አንቀፅ 1 እስከ 5 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ቅሬታ የፈጠረው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መልስ የማውጣት ጥያቄው ለመገናኛ ብዙሃን የቀረበ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

**47. ዋና አዘጋጅ የመሾምና የፕሮግራም ኃላፊ የማሳወቅ ግደታ**

1) በየጊዜው የሚታተሙ ኅትመቶች ዋና አዘጋጅነት የሚሾም ሰው ሥልጣን የሚታተሙትን ኅትመቶች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ እንዳይታተም ማድረግን ያካትታል፡፡ ይህን ሥልጣን የሚገድቡ ማናቸውም አሰራሮች ወይም ስምምነቶች ውድቅና ፈራሽ ናቸው፡፡

2) በየጊዜው የሚታተመው ኅትመት ዋና አዘጋጅ በማንኛውም ምክንያት የተሟላ የሕግ ችሎታ የሌለው ከሆነ የተሟላ የሕግ ችሎታ ያለው ኃላፊ አዘጋጅ መሾም ይኖርበታል፡፡

Preliminary Draft

3) በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 2 መሠረት ለኃላፊነት የተሾመው ዋና አዘጋጅ በየጊዜው የሚታተመው ኅትመት ይዘት ውጤቶች ሙሉ የሕግ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ ታትሞ እንዳይወጣ የማድረግ ሥልጣን አለው፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ከንኡስ አንቀፅ 1-3 የተደነገገው ቢኖርም የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶችን ወይም የአክስዮን ድርሻ ያላቸው ሰዎችን ዋና አዘጋጅ ሆኖ መሾም አይከለከልም፡፡

5) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለሚያሠራጨው ፕሮግራም እና ዜና ኃላፊ አድርጎ የሚመድበውን ሰው ለባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለበት፡፡ በኃላፊነት የተመደቡት ሰዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ የእያንዳንዱ ሰው የኃላፊነት ድርሻ በግልጽ ተለይቶ መገለጽ አለበት፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ የባለፈቃዱን ኃላፊነት አያስቀረውም፡፡

**48. በኅትመትና የብሮድካስት ሥርጭት ላይ የሚገለፁ ነገሮች**

1) ማንኛውም አይነት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት በእያንዳንዱ እትም ላይ የአሳታሚውን፣ የአታሚውን፣ የዋና አዘጋጁን ስምና አድራሻ፣ የኅትመቱን ቅፅ፣ ቁጥር፣ ኅትመቱ የሚወጣበትን ጊዜ እና ታትሞ የወጣበትን ቀን፣ ወርና አመተ ምህረት በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

2) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የፕሮግራም ሥርጭት መጀመሪያና ማብቂያ ላይ፡-

ሀ) የጣቢያውን ስምና የተላለፈበትን ቀን፤ እና፣

ለ) የፕሮግራሙን መሪ ወይም አዘጋጅ ስም፤

መግለጽ አለበት፡፡

Preliminary Draft

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቴሌቪዥን አገልግሎት ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የፕሮግራም ሥርጭት የጣቢያውን ምልክት ማካተት አለበት፡፡

49. **ያለ ክፍያ የሚሰጡ ቅጅዎች**

1) ማንኛውም በአዲስ አበባ የሚሰራጭ ወይም የሃገር አቀፍ ስርጭት ያለው በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ታትሞ በወጣ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም ሁለት ቅጂዎች ያለ ክፍያ ለብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት ኤጀንሲ መስጠት አለበት፡፡

2) በየጊዜው የሚወጣው ኅትመት ስርጭት በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የተወሰነ ከሆነ ታትሞ በወጣ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም ሁለት ቅጂዎች ያለ ክፍያ ለክልሉ ቤተ-መዛግብት ወይም ማስታወቂያ ቢሮ መስጠት አለበት፡፡

50. **የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች**

1) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲሁም በሕገ መንግሥቱና በሌሎች የጋራ አገራዊ ጉዳዩች ዙሪያ ለጋራ መግባባት አስተዋፅኦ የሚያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት የመስጠት፤

ለ) በዕለቱ ፕሮግራም ውስጥ አካባቢያዊ፣ ክልላዊና አገራዊ ዜናዎችን የማቅረብ፤

ሐ) ከቀጥታ ሥርጭት ውጭ ማናቸውም ፕሮግራም በጣቢያው ከመሠራጨቱ በፊት ሕግን የሚያከብር መሆኑን የማረጋገጥ፤



Preliminary Draft

መ) በፕሮግራም ሥርጭቱ ተገቢና ጨዋ የቋንቋ አጠቃቀም ተግባራዊ የማድረግ፤

ሠ) በፕሮግራም መርሀ-ግብሩ መሰረት ፕሮግራሞችን የማሠራጨት፤ በመርሀ ግብሩ መሠረት ማሠራጨት ካልተቻለ አስቀድሞ የማሳወቅ፤

ረ) በማስታወቂያ አዋጅ ስለማስታወቂያ እና ስፖንሰርሽፕ መግለጫ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የማክበር፤

ሰ) ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች እንዲሁም ለፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ውጤቶች መብት ጥበቃ የወጡ ሕግጋትን የማክበር፡፡

2) ማንኛውም የትምህርት ማሠራጫ ጣቢያ ለመማር ማስተማር ሂደት ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ማሠራጨት ይኖርበታል፡፡

## 51. የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች

ማንኛውም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

ሀ) ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ርዕዮተ-ዓለምና አመለካከትን ጨምሮ የሃገሪቱ ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ዜናና ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ለ) የሕዝብን ጥቅም ለሚመለከቱ ሃገራዊና አለም አቀፍ ጉዳዮች ሽፋን በመስጠት ከፍተኛ የሙያ ደረጃ የሚጠይቀውን ፍትሃዊነት፣ ገለልተኛነት፣ ሚዛናዊነትና ምክንያታዊነትን በማሟላት ሁሉን አቀፍ ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ሐ) የማኅበረሰብ ልማት፣ ጥቅሞችና የጋራ እሴቶችን የተመለከቱ መረጃዎችንና ፕሮግራሞችን ለሕዝብ ማድረስ፤

Preliminary Draft

መ) በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦችን አንድነት የሚያንፀባርቅ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ሠ) የሕዝቡን ባህልና ጥበባዊ እሴቶች የማስተዋወቅና የማጎልበት፤

ረ) በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የማገልገል፤

ሰ) ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተያያዙ አወዛጋቢ ጉዳዮችን ሽፋን ሲሰጡ በተመሳሳይ ፕሮግራም ወይም በሌላ ቀጣይ ፕሮግራም የተለያዩ አመለካከቶችን ለማስተናገድ ምክንያታዊ ጥረት የማድረግ፡፡

## 52. የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች

1) ማንኛውም የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ለትርፍ ዓላማ የተቋቋመ ቢሆንም ከእለት ፕሮግራሙ ውስጥ እስከ 10 በመቶ ለሃገር ውስጥ ይዘት የማዋል ግዴታ አለበት፡፡

2) የንግድ ብሮድካስተሮች የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን በዴሞክራሲያዊ ግልፅነትና ተጠያቂነት መርሆዎች መሠረትና የማኅበረሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ መረጃዎችንና ፕሮግራሞችን ለሕዝብ ማድረስ አለባቸው፡፡

## 53. የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች

ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

Preliminary Draft

ሀ) የማኅበረሰቡን የሰላም፣ የልማት፣ የማኅበራዊ እና የመልካም አስተዳደር ፍላጎት መሠረት አድርጎ የመሥራት፤

ለ) የማኅበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህልና ጥበባዊ እሴቶች ማስተዋወቅና ማጎልበት፤

ሐ) በኘሮግራም ዝግጅት የማኅበረሰቡን አባላት ማሣተፍ፤

መ) ሌሎች የብሮድካስት አገልግሎቶች ሊያሠራጩ ያልቻሉትን የማኅበረሰቡን የጋራ ጉዳዩች የሚመለከቱ ኘሮግራሞችን ማሠራጨት፤

ሠ) ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ለማሠራጫ ጣቢያው አገልግሎት ማዋል፤

ረ) ለማኅበረሰቡ ጠቀሜታ ያላቸውና ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረጉ አስፈላጊ መረጃዎችንና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የማኅበረሰቡን የመረጃ አጠቃቀም ባህልና እውቀት የማዳበር፤

### 54. የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች

ማንኛውም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1) በባለፈቃዶች መካከል የሚደረግ የፕሮግራም ልውውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የፕሮግራም ቻናል ብቻ ፕሮግራሙን የማሠራጨት፤

2) በቀጥታ ሥርጭት የሚሠራጩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን ሲያቀርብ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ለመከታተል እንዲችሉ የፕሮግራሙን ይዘት በተጓዳኝ መስኮት በምልክት ቋንቋ የማቅረብ፤

Preliminary Draft

3) በጽሁፍ የሚያቀርባቸውን አስፈላጊ መረጃዎች በድምጽ አስደግፎ የማቅረብና በውጪ ቋንቋዎች ለሚቀርቡ ፕሮግራሞች በሃገር ውስጥ ቋንቋዎች በጽሁፍ ትርጉም የማቅረብ፡፡

## 55. ስለአገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የብሮድካስት አገልግሎት የሥርጭት ኘሮግራም

1) ማንኛውም አገር አቀፍ ሥርጭት ከሳምንታዊ ሥርጭት ጊዜው ቢያንስ 80 በመቶውን ለአገራዊ እና ለክልላዊ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

2) ማንኛውም ክልላዊ ሥርጭት ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው ከ70 እስከ 80 በመቶውን ክልሉን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

3) ማንኛውም አካባቢያዊ ሥርጭት ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው ከ70 እስከ 80 በመቶውን አካባቢውን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ ክልላዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

4) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ጥራቱን የጠበቀ እና የተለያየ ይዘት ያላቸውን አገራዊ ፕሮግራሞች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለዜና፣ ለወቅታዊ ጉዳይ፣ ለትምህርታዊ፣ ለመዝናኛና ለሌሎች ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ተገቢውን የአየር ሰአት መመደብ ይኖርበታል፡፡

## 56. አስቸኳይ መንግስታዊ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት



Preliminary Draft

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ፡-

1) ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት የሚያናጋ ሁኔታ፣

2) የተፈጥሮ አደጋ በማጋጠሙ ወይም የሕዝቡን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሽኝ በሽታ፣

በመከሰቱ ምክንያት የፌዴራል መንግስት ወይም ማንኛውም የክልል መንግሥት የሚሰጠውን አስቸኳይ መግለጫዎች ያለክፍያ ማሠራጨት አለበት፡፡

**57. ስለማሳወቅ**

1) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ለውጦች ሲያደርግ ለውጦችን ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

ሀ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲጀመር፤

ለ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲቋረጥ፤

ሐ) የመርሀ ግብር ለውጥና የሥርጭት ሰዓት ለውጥ ሲያደርግ፤

መ) የጣቢያውን ስም፣ ምልክትና አድራሻ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፤

ሠ) የጣቢያውን ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ወይም የፕሮግራም ኃላፊ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፡፡

2) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ከማድረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅና ተገቢውን ፈቃድ ወይም ይሁንታ ማግኘት አለበት፤

Preliminary Draft

ሀ) የጣቢያውንም ሆነ የጣቢያውን የአክስዮን ባለድርሻዎች የአክስዮን ድርሻ መጠን ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ወይም ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ ወይም ሌላ የመገናኛ ብዙሃን የንግድ ማኅበርን ለመግዛት ወይም ለመዋሀድ እንዲሁም መሰል ለውጥ ለማድረግ፤

ለ) የውጪ ብሮድካስተሮች የሚያሠራጩትን ፕሮግራም ተቀብሎ ለማሠራጨት፤

3) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ የኦዲት ሪፖርት፣ የጣቢያውን የፋይናንስ ምንጭ ማስረጃ እና ዓመታዊ የወጪና ገቢ ሪፖርት የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4) የጣቢያውን የአየር ሰዓት ለሌላ ተባባሪ የፕሮግራም አቅራቢ የሚያስተላልፍ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተባባሪ የፕሮግራም አቅራቢዎች ተገቢ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥና የስም ዝርዝርና የሚያሠራጩትን የፕሮግራም ዓይነት የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ ይኖርበታል።

Preliminary Draft

### 58. ፕሮግራም ቀርጸ ስለመያዝ

1) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ማንኛውንም ያሠራጨውን ፕሮግራም ለ30 ቀናት ቀርጾ ማስቀመጥ አለበት፤ በፕሮግራሙ ውስጥ ቀደም ሲል የተቀረጸ ፕሮግራም ወይም ፊልም ተካቶ ከሆነ አብሮ መቀመጥና በተፈለገ ጊዜ ሊገኝ መቻሉ መረጋገጥ አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበ ቅሬታው አግባብ ባለው ሕግ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የፕሮግራም ቅጅውን ባለፈቃዱ ማቆየት አለበት።

3) ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለፈቃዱ የያዘውን ፕሮግራም ቅጅ በራሱ ወጪ ለባለሥልጣኑ ወይም በሕግ መሠረት ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የይዘት ክትትልና እርምጃ

### 59. መሠረታዊ መርሆች

1) በብሮድካስት ስርጭት ላይ የይዘት ቁጥጥር የሚደረገው አድማጭና ተመልካችን ከጉዳት ለመከላከልና እንደ ሸማችነታቸው ደግሞ ከሚያሳስቱ ማስታወቂያዎችና ካልተገቡ የንግድ ውድድሮች ለመጠበቅ ብቻ ነው፡፡

2) ይህ የይዘት ቁጥጥር በማንኛውም ሁኔታ ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ መብትና የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት በቅድመ-ምርመራ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ፤ ትክክለኛ መረጃ የማስተላለፍ መብትና ጥራት ያለው ፕሮግራም የመስራት መብት ላይ ያልተገባ ተፅእኖ ሳይፈጥር መካሄዱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

### 60. ጠቅላላ

1) በብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ኘሮግራም ወይም ዜና የሚከተሉትን ማክበር ይኖርበታል፡-

ሀ) ኘሮግራም ወይም ዜና የተለያዩ አመለካከቶችን በማንፀባረቅ አጠቃላይ ሕብረተሰቡን እንዲያገለግል ሚዛናዊና ከአድልዎ የፀዳ ሆኖ መቅረብ፤

Preliminary Draft

ለ) የሚሰራጨው ኘሮግራም ወይም ዜና ይዘትና ምንጭ እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አሰራጩ ሪፖርቱ ላይ ተገቢ ጥንቃቄ እንዲያደርግና ስህተት ሲገኝም እንዲያርም ይጠበቅበታል፤ ጥፋቶችን ለማረም የሚያስችል የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

2) በብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ኘሮግራም ወይም ዜና፣

ሀ) የማንኛውንም ሰው የግል ሕይወት የመከበር መብት የሚጥስ፤

ለ) የሰው ልጆችን ክብር ወይም ሥነ-ምግባርንና ጨዋነትን የሚፃረር፤

ሐ) በቀጥታ ጉዳት የሚያስከትል ወይም ለጤናና ለደኅንነት ጎጂ የሆነ ባህሪን የሚያበረታታ፤

መ) የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም እና ሰላምና ፀጥታ እንዲደፈርስ የሚቀሰቅስ፤

ሠ) ማንኛውም ሰው ዘርን፣ ዜግነትን፣ ብሔርን፣ ቀለምን፣ ኃይማኖትን፣ ጾታን፣ እድሜን ወይም የአእምሮ በሽታንና የአካል መጉደልን መሰረት በማድረግ እንዲጠላ፣ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል የሚቀሰቅስ፤

መሆን የለበትም፡፡

3) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጥቃት ወይም መሰል አሰቃቂ ወይም አስደንጋጭ ሁኔታዎችን የሚዘግቡ መዋዕለ ዜና ወይም ፕሮግራሞችን ሲያሠራጭ በአቀራረባቸው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4) ባለሥልጣኑ በብሮድካስት አገልግሎት የሚሠራጩ ፕሮግራሞች የሚመሩበትን ዝርዝር የሥነ-ምግባር ደንብ ያወጣል፤ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶችም ለሥነ-ምግባር ደንቡ ተገዥ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 61. ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ደህንነት ስለመጠበቅ

Preliminary Draft

1) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በስነምግባር፣ በስነልቦና ወይም በአካል ሊጎዳ የሚችል ከአመፅና ብጥብጥ፣ ከወሲባዊ ቅስቀሳና ከአልተገባ ቋንቋ ጋር የተያያዘ ይዘት ያለው የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራምን፡-

ሀ) ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ሊመለከቱና ሊያዳምጡ በሚችሉበት ሰዓት ማስተላለፍ የለበትም፤ ወይም፣

ለ) ከማሠራጨቱ በፊት የፕሮግራሙን አድማጭ ወይም ተመልካች የዕድሜ ደረጃ አስቀድሞ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች በማሳወቅ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራሞችን ሊያዳምጡና ሊመለከቱ አይችሉም የሚባለው ጊዜ ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 11 ሰዓት ድረስ ነው፡፡

## 62. ኃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞች

1) ኃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞችን የሚያሰራጭ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለሁሉም ኃይማኖቶችና እምነቶች ተገቢ ክብር እንደተሰጣቸው ሊያረጋገጥና የኃይማኖት እና የእምነት ነጻነትንና መሠረታዊ ሰብዓዊ መብትን ሊጠብቅ ይገባል፡፡
2) ማንኛውም ኃይማኖት ተኮር ፕሮግራም በኃይማኖቶች መካከል የእርስ በርስ ግጭት ማነሳሳት፣ የሌሎችን ኃይማኖት ወይም እምነት ማንኳስስ፣ ወይም በኃይማኖቶች መካከል አለመቻቻል እንድፈጠር መቀሰቅስ የለበትም፡፡

## 63. የምርጫ ጊዜ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት

Preliminary Draft

1) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ተገቢ የሆነ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡ ነገር ግን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በርካታ መቀመጫዎች ያሏቸው እና ለምርጫው በርካታ እጩዎችን ያቀረቡ ዋነኛ ፓርቲዎች ከሌሎች ፓርቲዎች በተለዬ ሰፋ ያለ ሽፋን የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ቢሆንም የምርጫ ጉዳዮች ለውይይት ሲቀርቡ ሰፊና የተለያዩ የፓርቲዎች የፖለቲካ አተያይ ሊካተት ይገባል፡፡

2) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት፡ ፡ እያንዳንዱ ፓርቲ የሚገባውን የአየር ጊዜ ግልፅ በሆነና አስቀድሞ በተወሰነ ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር በሚያዘጋጀው ቀመር መሰረት ባለሥልጣኑ ይመድባል፡፡

3) በማንኛውም ሁኔታ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ነፃ የአየር ጊዜ የመስጠት ግዴታ ከሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ያነሰ መሆን አለበት፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

5) ለምርጫ ውድድር ማስታወቂያ የሚጠየቀው ክፍያ ለንግድ ማስታወቂያ ከሚጠየቀው ክፍያ ሊበልጥ አይችልም፡፡

Preliminary Draft

6) ነፃ የአየር ጊዜ የተሰጠው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ ለተሰራጨው ፕሮግራም፣ መግለጫ ወይም ማስታወቂያ ኃላፊ ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ የባለፈቃዱን ኃላፊነት አያስቀርም፡፡

**ክፍል ስድስት**

**አስተዳደራዊ ቅጣቶች**

**64. አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

1) በዚህ አዋጅ፣ በማስታወቂያ አዋጅ እና በወንጀል ሕግ የተደነገገው የቅጣት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅና የማስታወቂያ አዋጅ ድንጋጌዎችን፣ በዚህ አዋጅና በማስታወቂያ አዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ ወይም መመሪያን፣ የፈቃድ ሁኔታን በተላለፈ ወይም ባለሥልጣኑ የሰጠውን ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ባላከበረ የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪ ላይ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፤

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) አንድን ጉዳይ በተመለከተ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እርምጃ እንዲወሰድ ወይም ምንም ዓይነት ተጨማሪ ድርጊት እንዳይፈፀም ማዘዝ፤

ሐ) ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት እስከ 50ሺ. ብር የሚደርስ አስተዳደራዊ መቀጮ መጣል፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 መሠረት የእርምት እርምጃ እስከሚወስድ ድረስ የባለፈቃዱን ፈቃድ ማገድ ወይም የሕግ ጥሰት የተፈፀመበትን አንድን ፕሮግራም ማገድ ወይም በአንቀፅ 37 መሰረት የባለፈቃዱን ፈቃድ መሰረዝ ወይም የሕግ ጥሰት የተፈፀመበትን አንድን ፕሮግራም መሰረዝ፡፡

Preliminary Draft

2) ፍትሐዊነትንና ግልፅነትን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ መደበኛ የሆኑ ቅጣቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ ሲወስን ሥራ ላይ የሚያውለውን ሒደት ማሳተም አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ ከባድ የገንዘብ ቅጣት ወይም የፈቃድ መነጠቅ የሚያስከትል ቅጣት ተፈጻሚ ለማድረግ ሲወስን ባለፈቃዱ ጉዳዩ በግልፅ እንዲዳኝና ሕዝባዊ አስተያየት እንዲሰጥ የማድረግ አማራጭ ሊሰጠው ይገባል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ባለሥልጣኑ በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፤ ቦርዱም ቅሬታው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

5) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀፅ (3)፣ አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ (2) እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

6) ቦርዱ ጥያቄው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ግልባጭ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 65. ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

1) በአንጻራዊነት ቀላል ለሆኑ ግድፈቶች ባለሥልጣኑ ለብሮድካስተሩ በሚፅፈው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይታለፋሉ፡፡

2) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የፈቃዱ ጊዜ ሲያበቃ ፈቃዱን ማደስ ከፈለገ ሕግና መመሪያዎችን አክብሮ ባለመስራቱ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች ፈቃድ ማደስን

Preliminary Draft

አስመልክቶ ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው ውሳኔ ግንዛቤ ውስጥ እንደሚገቡ ግልፅ ሊደረግለት ይገባል፡፡

3) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ሕግና መመሪያዎችን አክብሮ የመስራት የኋላ ታሪኩ ደካማ ከሆነ ፈቃዱ ከመታደስ ይልቅ በግልፅ በድጋሜ ማስታወቂያ ሊወጣበት ይችላል፡፡

**66. የገንዘብ ቅጣትን ስለመደንገግ**

1) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ጥሰት ከባድ ከሆነ ወይም በአጠቃላይ ሕግና መመሪዎችን በማክበር ረገድ መሻሻል ካላሳየና ቀላል የሆኑ ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ካለው የገንዘብ ቅጣት ይጣልበታል፡፡

2) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የገንዘብ ቅጣት ሊጣልበት እንደሆነና ጥሷል የተባለውን ጉዳይ እንዲያውቅ ማድረግና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ የገንዘብ ቅጣት መጠን ሲወስን የሚከተሉትን ጉዳዮች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ) የጥሰቱን ክብደት፤

ለ) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ተደጋጋሚ ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ፤

ሐ) ባለፈቃዱ በሥርጭቱ ምክንያት ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ካለ፤

መ) የባለፈቃዱ አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፡፡

Preliminary Draft

4) የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ ባለሥልጣኑ የሚጥለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ከአጠቃላይ ካፒታሉ አንጻር ሲሰላ የባለፈቃዱን ህልውና ከባድ አደጋ ላይ ሊጥለው አይገባም፡፡

## 67. ፈቃድን ስለማገድ

1) የብሮድካስት ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በተደጋጋሚ የሚጥስና የጥሰቱም ክብደት እየጨመረ መምጣት ማሻሻያ እንደማያደርግ የሚያሳይ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ካመነ ፈቃዱን ሊያግደው ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረግ እገዳ በጽሁፍ ሆኖ እገዳው የተደረገበት ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ተገልጾ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡ ባለፈቃዱ ማሻሻያ የማያደርግ ከሆነ ፈቃዱ ሊሰረዝ እንደሚችል ግልፅ ሊደረግለት ይገባል፡፡

3) በተጣለበት እገዳ ቅር የተሰኘ ባለፈቃድ የእግዱ ትዕዛዝ በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፤ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## 68. ፈቃድን ስለመሠረዝ

1) ባለሥልጣኑ ፈቃድ መሰረዝን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችለው ባለፈቃዱ ወጥ በሆነ ሁኔታ አዋጁንና ደንቦቹን ባለማክበር እንዲሁም የባለሥልጣኑን ትዕዛዞች ባለመፈጸም ከባድ ጥፋት ከፈጸመ ብቻ ነው፡፡ የብሮድካስት ፈቃድ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ በባለሥልጣኑ ሊሰረዝ ይችላል፦



Preliminary Draft

ሀ) ባለፈቃዱ ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መደበኛ ሥርጭቱን ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ለ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) የሥርጭት ጣቢያው ያለበቂ ምክንያት ሥርጭቱን ወይም አገልግሎቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፤

መ) ጣቢያው ወይም ድርጅቱ እንዲዘጋ በፍርድ ቤት ሲታዘዝ፤

ሠ) ባለፈቃዱ በራሱ ፍላጎት ሥራውን ሲያቆም፤

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተጥሰው ሲገኙ፤

ሰ) ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 የተመለከተውን የክፍያ ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሸ) ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የባለቤትነት መስፈርት ድንጋጌዎችን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ፤ ይህንንም ለማሻሻል የማይችልና የማይፈልግ መሆኑ ሲረጋገጥ፡፡

2) ባለሥልጣኑ የፈቃድ መሰረዝ የሚያስከትል ቅጣት ተፈጻሚ ለማድረግ ሲወስን ባለፈቃዱ በጉዳዩ ላይ ያለውን ምላሽ በፅሁፍ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብና ጉዳዩ ላይ ሕዝባዊ አስተያየት እንዲሰጥ የማድረግ እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡ ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ የይዘት ጥሰቶችን እንደሚያሻሽል የሚያሳይ አሳማኝ ምክንያት ካላገኘና ሁለተኛ እድል ይገባዋል ብሎ ካላመነ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

3) በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የብሮድካስት ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፤ ቦርዱም ቅሬታው በቀረበለት በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ከቦርዱ ውሳኔ በኋላ ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሄድ መብት የተጠበቀ ነው፡፡

4) የብሮድካስት ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መደበኛ ሥርጭቱን ለመጀመር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው ስለመሆኑ አመልክቶ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ሥርጭቱን ለመጀመር የሚያስችል ከአንድ አመት የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

**ክፍል ሰባት**

**የይዘት ቁጥጥር ሒደት**

**69. ዝርዝር ደንቦች**

1) ባለሥልጣኑ መሠረታዊ ሕጎችን እንዴት እንደሚተረጉም በዝርዝር የሚያስረዱ መመሪያዎችን ማውጣት ያወጣል፡፡

2) ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ የማየት ሥልጣናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዝርዝር መመሪያዎቹ በሕግ ሥርዓቱ በቀጥታ እንዲተገበሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሆነው ሊወጡ ይችላሉ፡፡

**70. የቅሬታ ወይም የአቤቱታ አፈታት ሥርዓት**

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብን ቅሬታ ወይም አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ሕጋዊ እርምጃዎች**

Preliminary Draft

71. **መሠረታዊ መርሆዎች**

1) መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አመለካከቶችን በማንፀባረቅ አጠቃላይ ሕብረተሰቡን የሚያሳውቅ፣ የሚያስተምርና የሚያዝናና ጥራቱን የጠበቀ፣ ሚዛናዊና ከአድልዎ የፀዳ፣ ይዘቱና ምንጩ እውነተኛና ትክክለኛ የሆነ ይዘት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2) ሕጋዊ እርምጃዎች በሕግ መሰረት የሚከናወኑና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅን መብት በማያጠብ መልኩ የሚተገበሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

72. **የጉዳት ካሳ**

(1) በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰበት ሰው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 43 በተደነገገው መሰረት ተጠያቂነት ያለባቸው ሰዎች ላይ የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

(2) በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ድንጋጌዎችና በወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መሀከል ግጭት ከተፈጠረ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

73. **የስም ማጥፋት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት**

(1) የስም ማጥፋት የፍትሐብሔር እንጂ የወንጀል ተጠያቂነት የማያስከትል በመሆኑ፤ የስም ማጥፋት በማንኛውም መልኩ የእስር ቅጣት ሊደረግበት አይችልም፡፡

(2) የስም ማጥፋትን አስመልክቶ በመገናኛ ብዙሃን የሚጣለው የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ ከብር 300ሺ ሊበልጥ አይችልም፡፡ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ለሚደርስ የስም ማጥፋት ጉዳት የፍትሐብሔር ክስ ከተመሰረተ ፍርድ ቤት ትርፍ ባላገኙ መገናኛ ብዙሃን ላይ የጉዳቱን መጠን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ፍትሃዊ የካሳ ክፍያ

Preliminary Draft

ሊወስንና ትርፍ እያገኙ ባሉ መገናኛ ብዙሃን ላይ ግን ከብር 25ሺ እስከ 300ሺ የሚደርስ የህሊና የጉዳት ካሳ ሊወስን ይችላል።

(3) የሚከተሉት ሁኔታዎች በስም ማጥፋት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትሉ አይችሉም፡-

(ሀ) የመጉዳት ሃሳብ ከሌለና የንግግሩ ይዘት እውነተኛ የሆነ እንደሆነ፤

(ለ) ተጎጂው መረጃ እንዲሰጥ ተጠይቆ ባለመስጠቱ የተከሰተ ንግግር ከሆነ፤

(ሐ) የንግግሩን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ተቀባይነት ያላቸውን አካሄዶችና መንገዶች ሁሉ ተጠቅሞ ያገኘው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ በቅንነት በማመን ያደረገው ንግግር ከሆነ፤

(መ) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተደረገ ንግግር ከሆነ።

(4) የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች በስም ማጥፋት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትሉ አይችሉም፡-

(ሀ) በኢፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በፕሬዚዳንቱ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት የተደረገ ንግግርን አስመልክቶ የሚደረግ ንግግር ከሆነ፤

(ለ) ማንኛውም የፌደራልም ሆነ የክልል መንግሥታት ተሿሚዎች፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ በምክር ቤትም ይሁን በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው የተደረገ ንግግርን ወይም ውሳኔን አስመልክቶ የሚደረግ ንግግር ከሆነ፤

(ለ) በፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ በዳኞች፣ ጠበቆች፣ ተከላካይ ጠበቆች፣ ዓቃቢያነ ሕግ፣ ነገረ-ፈጅ፣ ወይም ምስክሮች የሚያደርጉት ንግግር፤ ወይም፣



Preliminary Draft

(ሐ) የሕግ ግዴታ ያለበትን ሰው የሚያደርገው ንግግር፡፡

**74. ስለ ቅጣት**

በወንጀል ሕጉ የተከለከሉ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፤ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም መገናኛ ብዙሃን በሚከተለው መልኩ የሕግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡-

(ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 23 እና 24 (ምዝገባ ፈቃድ) እና 32 (የማስፋፍያ ፈቃድ) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከ150ሺ ብር ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

(ለ) በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ሲሆን እና ምዝገባው ያልተካሄደው በባለሥልጣኑ ድክመት ከሆነ፤ በንኡስ አንቀፅ 1 ያለው ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ የገንዘብ ቅጣት አወሳሰን ላይ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ሲሆን የገንዘብ ቅጣቱ ከ15ሺ ብር በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

(ሐ) በዚህ አዋጀ በአንቀፅ 41 (በኅትመትና የብሮድካስት ሥርጭት ላይ የሚገለፁ ነገሮች) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ወይም ብሮድካስተር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ከብር 15ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

(መ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 40 (ዋና አዘጋጅ የመሾምና የፕሮግራም ኃላፊ የማሳወቅ ግደታ) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 15ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

Preliminary Draft

(ሰ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 50፣ 51 እና 52 (የተከለከሉ ተግባሮች-ስምማጥፋት-የህፃናት መብት) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ወይም ብሮድካስተር ከብር 100ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

(ረ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 39 መሰረት በኅትመቱ ላይ እንዲያወጣው የተላከለትን መልስ ወይም ማስተካከያ ያላወጣ ዋና አዘጋጅ ወይም የፕሮገራም አዘጋጅ እስከ ብር 15ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

(ሠ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 53 (በነፃ የማሰራጨት ግዴታ) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ባለፈቃድ ከብር 50ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

(ሸ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 22 (የባለቤትነት ገደቦች) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ባለፈቃድ እስከ ብር 200ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

(ቀ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 31 (የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ስለማይሰጣቸው ሰዎች) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ባለፈቃድ ከብር 50ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

(በ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 35 የተላለፈ ባለፈቃድ (የፈቃድ፣ ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ) ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፈላል፤ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከአመታዊ ክፍያ ወይም የፈቃድ ማደሻ ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

(ተ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 43 (ሰ) (የማስታወቂያ፤ስፖንሰርሽፕ መግለጫ) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ባለፈቃድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ከብር 30ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። የሌላውን ምርት ወይም አገልግሎት በማጥላላት ወይም በማነኳሰስ ማስታወቂያ ማስተላለፍ እና የተከለከሉ ማስታወቂያዎችን በሚያስተላልፍበት ጊዜ ሲሆን ግን፤ ባለፈቃዱ ያለማስጠንቀቂያ እስከ 30 ሺ. ብር ይቀጣል።

Preliminary Draft

## 75. የእገዳ እርምጃዎችን ስለመውሰድና እግድ ስለመጣል

1) በሌላ ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም በዚህ አንቀፅ ከተደነገገው ውጭ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሊታገድ አይችልም፡፡

2) እንደነገሩ ሁኔታ የፌደራል ወይም የክልል አቃቤ ሕግ በብሔራዊ ደኅንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በየጊዜው የሚወጣ ሕገ ወጥ ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የኅትመት ውጤቱ ወይም የብሮድካስት አገልግሎቱ እንዳይሰራጭ ፍርድ ቤት እንዲያዝ ማመልከት ይችላል፡፡

3) አቃቤ ሕግ ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ ሆኖም አቃቤ ሕግ አንድን በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ወይም ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ከስርጭት እንዲታገድ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው በተሰጠ በ48 ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ሕጉ የእገዳ ማስታወቂያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ የእገዳ እርምጃውን የሚያፀድቅ መሆን አለመሆኑን በውሳኔ ማሳወቅ አለበት፡፡

4) ፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚወጣው ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት እንዲታገድ በአቃቤ ሕግ የተሰጠው ትእዛዝ ሲቀርብለት፡-

ሀ) በየጊዜው የሚወጣው ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሕገ ወጥና ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ካገኘው የአቃቤ ሕጉን ትእዛዝ በማፅደቅ አቃቤ ሕጉ የማገድ እርምጃ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ክሱን እንዲመሰርት ማመልከቻ እንዲያቀርብ ማዘዝ አለበት፡፡ አቃቤ ሕግ በተሰጠው ትእዛዝ

Preliminary Draft

መሰረት ካልፈጸመ ፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት እንዲያዝ ወይም ስርጭቱ እንዲቋረጥ የሰጠውን ትእዛዝ ያነሳል፡፡

ለ) በየጊዜው የሚወጣው ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሕግን የማይተላለፍና ከፍተኛ ጉዳትን የማያስከትል ሆኖ ካገኘው በአቃቤ ሕጉ የተሰጠውን የእገዳ ትእዛዝ ውድቅ በማድረግ የታገደው ኅትመት እንዲለቀቅ ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትእዛዝ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ካልታገደ በስተቀር ትእዛዙ በተሰጠ በ72 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ይፈጸማል፡፡

5) በየጊዜው የሚወጣው ኅትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ላይ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ ፍርድ ቤቱ ኅትመቱ እንዲያዝና እንደአስፈላጊነቱ ቀጣይ እትሞች ከማውጣት እንዲታገድ ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት እንዲታገድ በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 3 መሰረት የሰጠውን ውሳኔ ለመሰረዝ ይችላል፡፡

6) በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ስርጭት ላይ የሚሰጥ የእገዳ ትእዛዝ ለትእዛዙ መነሻ የሆነውን አንቀፅ ወይም አንቀፆች፣ የኅትመቱን ቅፅ፣ ጽሑፉ የወጣበትን እትም መግለጽ አለበት፡፡

7) በየጊዜው በሚወጣ ኅትመት ላይ የሚሰጥ እገዳ ለስርጭት በተዘጋጁ ኅትመቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የእገዳ ትእዛዙ በፖሊስ አማካይነት ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

8) ዓቃቤ ሕግ በዚህ አንቀፅ የተሰጠውን ሥልጣን አግባብ በሌለው መንገድ የተጠቀመበት እንደሆነ በሕግ ይጠየቃል፡፡ ግለሰቡ ላይም አስተዳደራዊና የገንዘብ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡ በእገዳው ምክንያት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት ለደረሰበት ጉዳት መንግሥት የሞራልና የጉዳት ካሳ ይከፍላል፡፡

Preliminary Draft

**ክፍል ዘጠኝ**

***ሥነ-ሥርዓታዊ ጉዳዮች***

**76. ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዙ ክሶች ስለሚቀርቡበትና ስለሚሰሙበት ሁኔታ**

1) በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የወንጀል ድርጊት በመፈፀም የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 59 (2) እና (3) ድንጋጌዎች መሰረት ለተጨማሪ ምርመራ በእስር እንዲቆይ ሳይደረግ ክሱ በቀጥታ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡
2) ክሱን ለመስማት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻው በቀረበለት በ15 ቀናት ውስጥ ክሱ እንዲሰማ ማድረግ አለበት፡፡
3) ፍርድ ቤቱ ክሱ ከመሰማቱ ቢያንስ ከአምስት ቀናት በፊት የክሱን ማመልከቻ ግልባጭ ወይም ቅጂ እንዲሁም የቀረቡ ማስረጃዎች ካሉ ለተከሳሹ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡
4) ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት ክሱ መሰማት ከጀመረበት ቀን አንስቶ እጅግ ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፍርድ መስጠት ይኖርበታል፡፡
5) ተከሳሹ በአድራሻው ባለመገኘቱ የተነሳ መጥሪያውን ለማድረስ ያልተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሰባት ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን የሚገልፅ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲወጣ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
6) ተከሳሹ በሌለበት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 77 መሰረት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**77. ስለ ይግባኝ**

1) በተሰጠው የቦርድ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡



Preliminary Draft

ውሳኔውን የሰጠው ቦርድም አመልካቹ ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ የውሳኔውን ግልባጭ ለአመልካች መስጠት አለበት፡፡

2) በቦርዱ ውሳኔ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን የሕግ ጉዳዮችን በመመርመር የተገደበ ነው፡፡

3) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙ በቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4) ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤትም አመልካቹ ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ የፍርዱን ግልባጭ ለአመልካች መስጠት አለበት፡፡

5) ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙ በቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

**78. ስለ ይርጋ**

1) በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 28(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈጸሙ የወንጀል ጥፋቶች ጎትመቶቹ ከተሰራጩበት ወይም ከተላለፉበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክሶቹ ካልቀረቡ በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ፡፡

2) በብሮድካስት አማካይነት ለሚፈፀም ጥፋት ጥፋቱ የተፈፀመበት ፕሮግራም ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የወንጀል ክስ ካልተመሰረተ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

Preliminary Draft

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 79. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1) ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ተቋቁሞ በየጊዜው የሚወጣ የኅትመት ስራ በማካሄድ ላይ የሚገኝ ማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 23 በተመለከተው መሰረት መመዝገብና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2) የአናሎግ ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የዲጂታል ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ተደርጎ የአናሎግ ቴሌቪዥን ብሮድካስት ሙሉ በሙሉ እስከሚቋረጥበት ጊዜ ድረስ የአናሎግ እና የዲጂታል ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎትን ጎን ለጎን ማሠራጨት ይኖርበታል፡፡
3) ማንኛውም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ የዲጂታል ብሮድካስት ሽግግርን የተመለከተ ፕሮግራም እና ማስታወቂያ ለሕዝብ ለማቅረብ የሚረዳ ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት፡፡
4) የአናሎግ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የጋራ የብሮድካስት ኔትወርክ አገልግሎት ስለሚያገኙበት፣ የተመደበላቸው ነባር የሬዲዮ ሞገድ ስለሚሰረዝበት እና ተለዋጭ ፈቃድ ስለሚያገኙበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡
5) ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሰረት የተሰጡ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዶች እንደፀኑ ይቆያሉ፤ ሆኖም ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለፈቃዱ አደረጃጀቱን በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲያሻሽል ይደረጋል፡፡

### 80. ከአዋጁ ጋር ስለሚቃረኑ ሕጎች

Preliminary Draft

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ትእዛዝ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**81. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

1) በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ተላልፈዋል፡፡

2) ማስታወቂያን በተመለከተ በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሰረት ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፡፡

**82. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) የባለሥልጣኑ ቦርድ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የሚከተሉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፤

ሀ) ዝርዝር የፈቃድ ሁኔታ በተመለከተ፤

ለ) የብሮድካስት ማሰራጫ መንገዶች የፈቃድ መስፈርትና ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በተመለከተ፤

ሐ) በማስታወቂያ ላይ የሚገለጹ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በተመለከተ፤

መ) የአመልካቾችን ብቃት ለመመዘን የሚያስችለው ዝርዝር መስፈርት በተመለከተ፤

ሠ) ለልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የአየር ሰዓት አመዳደብን በተመለከተ፤

ረ) ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ማሠራጨት በተመለከተ፤



Preliminary Draft

ሰ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሚወስነውን የድልደላ ቀመር እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አድርጎ የሚወጣ ለምርጫ ጊዜ መግለጫ ሥርጭት የሚውል ነፃ የአየር ጊዜ አፈፃፀምን በተመለከተ፤

ቀ) የቅሬታ ወይም የአቤቱታ አቀራረብና አፈታት መሠረታዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ፤

በ) እርማት ወይም መልስ የመስጠት መብትን አፈፃፀምን በተመለከተ።

**83. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

1) የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 እና የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል። ነገር ግን በአዋጅ ቁጥር 590/2000 ምዕራፍ ሦስት ስር የተደነገጉት የመረጃ ነፃነት ድንጋጌዎች የመረጃ ነፃነት አዋጁ ራሱን ችሎ እስኪወጣ ድረስ እንደጸኑ ይቆያሉ።

2) የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**84. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የወጡና ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረኑ ሕጎች በሌላ ሕግ እስኪተኩ ድረስ እንደፀኑ ይቆያሉ።

**85. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ------ ቀን.......... 2011 ዓ.ም

ወ/ሮ ሳሕለ ወርቅ ዘውዴ

Preliminary Draft

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Preliminary Draft